የቅንጅት ድጋፍ አስተባባሪ ድርጅት በታላቋ ብሪታንያ
Coalition for Unity & Democracy Party Support Organization - UK (KSOUK)

# የአንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ ፓርቲ መመስረት፣ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ለሚደረገው ትግል ታላቅ ተስፋ ነው፣

የቅንጅት የድጋፍ ድርጅት በዩኬ አባላት፣ አንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲን ለመመስረት የተደረጋውን ጥረት በቅርብ ስንከታተል ቆይተናል። በመጨረሻም ከብዙ ድካምና ውጣ ውረድ በኋላ የምስረታውን የምስራች የሰማነው በታላቅ ደስታ ነው።

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የፓሪቲው መሪ ሆና መመረጧና ሀላፊነቱን በመቀበሏ የተሰማንን ደስታ እየገለጽን፣ እህትነቷና ወጣትነቷ፣ በሚጠብቀን አስቸጋሪና ፈታኝ ትግል ወቅት፣ የጥንካሬ የተስፋ ምንጭ ሆኖ ሲጠቅም ለማየት ያለን ጉጉት ከፍተኛ ነው።

በአንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲ፣ በአመራር ደረጃ፣ በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴና በምክር ቤት፣ አባልነት በመመረጥ፣ የመስራች ጉባዔውን አደራ ለተቀበሉ ወገኖቻችን፣ ያለንን ክፍተኛ አክብሮት ለመግለጽ እንወዳለን።

ዛሬ ለአንድ አፍታ ቆም ብለን ሐገራችን ኢትዮጵያ ያለችበትን ሁኔታ ስንመለከት፣ በአንድ በኩል በሚሊዮን የሚቆጠሩ ልጆቿ ለርሀብ አደጋ የተጋለጡ ሲሆን ፣ በሌላ መልኩ የተፈጠረው የዋጋ ግሽበት ሕዝቡ ሊሸከመው ከማይቻልበት ደረጃ ደርሷል። በሐገር ደህንነት ስም የተጀመረው የሱማሌ ወረራ፣ ማጠፊያው ጠፍቶ ለበርካታ ችግሮች መንስዔ እዩሆነ ነው። የሐገራችን ምዕራብና የሰሜን ምዕራብ ክፍል ሰፊ መሬት፣ የቀረው ቀርቶ ለይስሙላው "ፓርላማ" እንኳን ሳይቀርብ፣ በሥልጣን መቆየትን ለማመቻቸት በታለመ የውስጥ ለውስጥ የፖለቲካ ውሉታ፣ ለበአድ ሐገር አሳልፎ የሚሰጥ ስውር ውል ተፈርሟል። በሰሜኑም የሐገራችን ክፍል ለአለፉት አመታት የዘለቀው ከፍተኛ የጦርነት አደጋ ውጥረት አሁንም እንደቀጠለ ነው።

በዚህ አስቸጋሪ ወቅት የአንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲ መወለዱ ታላቅ የምስራች ሆኖ ሳለ፣ ይህ ጊዜ የማይሰጥ ከፍተኛ አደጋ በአንጃበበባት ሐገር፣ የተቃዋሚ ፓርቲ ሆኖ የተቃዋሚ ፖለቲካ ማካሄድ፣ ምን ያህል ከፍተኛ ሀላፊነት መሸከም እንደሆነ እንገነዘባለን። ይህንን ዜጋዊና ታሪካዊ ሀላፊነት ለመወጣት ደግሞ ብልህነትን፣ አርቆ ማስተዋልን፣ መቻቻልን፣ ትግስትንና ከሁሉ በላይ ደግሞ ከፍተኛ የመንፈስ ጥንካሬን እንድሚጠይቅ ይሰማናል። በዚህ ፈታኝ የትግል ዘመን ፍትህና ዴሞክራሲ የሰፈነባትን ኢትዮጵያ ለመመስረት የአንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲ፣ በየፈርጁ ለሚያደርገው ጥረት፣ በምንችለው ሁሉ የመርዳት ግዴታችንን ለመወጣት ዝግጁ መሆናችንን ልናረጋግጥ እንወዳለን።

የግንቦት 97 የዴሞክራሲና የነጻነት መንፈስ ለዘላለም ይኑር!!!
የቅንጅት ድጋፍ ድርጅት ሥራ አስፍጻሚ ኮሚቴ፣
ለንደን፣

1Crowndale Road London NW1 1TU Tel/Fax: 020 7168 9893 E-mail: kinijit97@yahoo.co.uk